አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

_________ ዓመት ቁጥር _________
አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

_________ Year No. _______
Addis Ababa December 10,2016

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፵፰/፪ሺ፱**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፰/፪ሺ፱ ገጽ ———**

**CONTENTS**

**PROCLAMATION NO.48/2016 ADDIS ABABA CITY GOVERN MENT PLAN COMMISION ESTABLISHMENT PROCLAMATION PAGE ————**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፰/፪ሺ፱

አዲስ አበባ ከተማ የሀገሪቱና የአፍሪካ መዲና፣እንዲሁም የአለም አቀፍ ዲፕሎማሲና የሀገሪቱ ትራንስፎርሜሽን ማዕከል በመሆን የምትጫወተውን ሚና በዓለም አቀፍ ደረጃ በላቀ ሁኔታ ተወዳዳሪና መስህባዊ መሆን የሚያስችለው ተገቢ ተቋማዊ ማዕቀፍ አሰራር እንዲኖራት ማድረግ በማስፈለጉ፤

የፕላን መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚያደርግ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ሥርአት በመዘርጋት ለአፈጻጸም የሚያመቹ፣ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ ወቅታዊ ፕላኖችን የሚያዘጋጅና የሚተግብር እንዲሁም የሚመራና የሚቆጣጠር የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ማቋቋም ይህንን ለማሳካት እንደሚረዳ የታመነበት በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 14 (1) (ሀ) በተደነገገው መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## PROCLAMATION NO.48/2016 ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT PLAN COMMISION ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to ensure the presence of proper institutional framework and operations enabling Addis Ababa to make it more competitive and attractive in the roles it has been playing as the capital city of the country and Africa as well as a centre of international diplomacy and the transformation of the country;

WHEREAS, it has been believed that this can be attained by establishing an executive organ of the City Government empowered to prepare , apply, direct and regulate contemporary plans which are optimal for implementation, mutually reinforcing and interdependent as well as to lay down a transparent and accountable system whereby plan information is provided for users;

NOW, THEREFORE, the City Council of Addis Ababa, in accordance with Article 14(1) (a) of the Revised Addis Ababa city Government Charter Proclamation No. 361/2003, has hereby promulgated this Proclamation.

ያንዱ ዋጋ ———
Unit Price ———

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ 2445
Addis Negari Gazeta P.O.BOX 2445

## ክፍል ሁለት
## የኮሚሽኑ መቋቋም፣ተጠሪነትና አደረጃጀት

**፫. መቋቋም እና ተጠሪነት**

1) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ህጋዊ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2) የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መስሪያ ቤት**

1) የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በከተማው ውስጥ አመቺና ተደራሽ በሆነ ሥፍራ ይሆናል፤
2) ኮሚሽኑ ለሥራው አደረጃጀትና ስኬታማ ክንውን በሚያስፈልገው ደረጃና መጠን ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ይኖሩታል፡፡

**፭. አደረጃጀት**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡-

1) በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ምክር ቤት የሚሾም ኮሚሽነር፤
2) በከንቲባው የሚሾሙ ምክትል ኮሚሽነሮች፤
3) የዋና መስሪያ ቤትና የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች አደረጃጀቶች፤ እና
4) ሀሳብ አመንጪ እና አማካሪ ቦርድ፡፡

## ክፍል ሶስት
## የኮሚሽኑ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

**፮.አላማ**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

1) የከተማው እድገትና ልማት የሚመራበትና የሚቀናጅበት የጸደቀ ፕላን ወጥና ውጤታማ ተፈፃሚነት የማረጋገጥ፤
2) ፕላን ማዘጋጀት፣ ማሻሻል፣ማጣጣምና መተግበር ፍትሀዊ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ባለበት ስርዓት እንዲመራ የማድረግ፤
3) የከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር የአቅም ግንባታ ሥራ የመስራት፤ እና
4) በሙያዊ፣በቴክኒካዊና በሌሎችም አግባብ ባላቸው ወቅታዊ መረጃዎች የሚበለጽግ ተደራሽና ዘመናዊ የፕላን ስነዳና መረጃ ስርዓት የመዘርጋት፡፡

## Part Two
## Establishment, accountability and Organization of the Commission

**3. Establishment and accountability**

1) The Addis Ababa City Government Plan Commission is hereby established as one executive public office of the City Government having legal personality;
2) The Commission shall be accountable to the Mayor.

**4. Head Office**

1) The head office of the Commission shall be situated in a convenient and accessible place of the City;
2) The Commission shall have as many branch offices as the level and volume of its work organization and successful performance requires.

**5.Organizational structure**

The Commission shall have the following organizational structures:

1) the Commissioner proposed by the Mayor and appointed by the City Council;
2) Vice Commissioners appointed by the Mayor;
3) structures of the head office and branch offices, and the necessary human resource; and
4) Think tank & Advisory Board.

## Part Three
## purpose, Powers and Functions of the Commission

**6. Purposes**

The Commission shall have the following purposes:

1) to ensure the consistent and effective implementation of an approved plan by which the growth and development of the city is regulated and integrated;
2) to lay down equitable, transparent and accountable system whereby the preparation, amendment, adjustment and implementation of a plan is regulated;
3) to undertake to work for the capacity-building of the preparation and implementation of urban plan; and
4) To lay down accessible and modern system of plan documentation and database that shall be enriched by professional, technical and relevant contemporary information.



አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ 2445
Addis Negari Gazeta P.O.BOX 2445

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፰/፪ሺ፱ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡-

፩) "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪) "አስተዳደር/የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫) "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፬) "ፕላን/የከተማ ፕላን" ማለት እንደየአግባቡ የከተማው መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን የመሠረተ ልማት ግንባታ ቅንጅት ፕላን ወይም የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን የሚያጠቃልልነው፤

፭) "ኮሚሽን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደ ፕላን ኮሚሽን ነው፤

፮) "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (4) የተመላከተው የኮሚሽኑ ሃሳብ አመንጪና አማካሪ ቦርድ ነው፤

፯) "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰) በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያካትታል፡፡

## Part One
## General provisions

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Addis Ababa City Government Plan commission Establishment Proclamation No. 48/2016".

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation,

1) "City" means the Addis Ababa City;
2) "government/City government" means the Addis Ababa city government;
3) "Mayor" means the Mayor of the City;
4) "Plan/urban plan" means that which incorporates, as appropriate, the structural plan, local development plan, integrated infrastructural plan as well as medium-term and long-term social and economic development plan of the city;
5) "Commission" means the Addis Ababa City Government Plan Commission established under Article 3 Sub-Article (1) of this Proclamation;
6) "Board" means the think tank and Advisory Board of the Commission stipulated under Article 5 Sub-Article (4) of this Proclamation;
7) "Person" means any natural person or juridical person;
8) Whatsoever is stipulated in the masculine gender shall include the feminine gender.

## ፯) ስልጣንና ተግባር

፩) ኮሚሽኑ በስራው መስክ የሚከተሉት የወል ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) ከፌደራልና ከከተማው አስተዳደር ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር የሚጣጣሙ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፤ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ የፌደራል መንግስት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎችና ስልቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የፕላን ዝግጅትና አተገባበር የጥናትና ምርምር ሥራዎች ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤

መ) የሕዝብ ተግባቦትና ስርፀት ስራዎችን ያከናውናል፤ ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ስነዳና ስርጭት ቋት ያደራጃል፣ጥቅም ላይ ያውላል፤

ሠ) አስፈላጊውን የሰው ኃይል በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፣) (ሠ) የተደነገገው ቢኖርም፣

፩) ከመደበኛው የኮሚሽኑ የሰው ሀይል ስራ ስምሪት አቅም በላይ የሆነ የፕላን ዝግጅት፣ጥናትና ምርምር፣ የአቅም ግንባታ ስራ ፣ወዘተ ሲያጋጥመው፣ ስራውን ለማከናወን የሚያስችል እንዳስፈላጊነቱ ፕሮጀክት በመቅረፅ ለከንቲባው ያቀርባል፤ሲፀድቅም ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል በጊዜያዊ ውል አመቺ የስራ ሁኔታ በመቅ ጠር ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደርጋል፤

## 7. Powers and Functions

1. In its field of activity, the commission shall have the common powers and functions; to:

a) initiate policies and legislations in conformity with the policies and laws of the federal and city governments; prepare plan and budget, and implement same when endorsed;

b) ensure the implementation of the laws, policies, standards and strategies of the federal government concerning urban plan within the city ;

c) carry out activities of plan preparation and implementation ;and gather, process and disseminate data;

d) carry out communication and research activities, and organize and make available a pool of data documentation and dissemination by using accessible modern technology;

e) employ, administer and fire the necessary human resource in accordance with the Public Service law of the city government;

f) notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) (e ) of this Article, the commission:

1) it shall conduct study and research, capacity-building, etc. that goes beyond the capacity of its ordinary work engagement when the Commission encounters an activity of plan preparation, formulate and submit to the Mayor a project enabling it to carry out such activity; and, upon the approval of the project, implement it by deploying the required human resource based on temporary employment contract stipulating suitable conditions of work;

፪) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (1)(ረ)(1) የተደነገገው ቢኖርም፣ልዩ የሙያ ችሎታ ወይም ብቃት የሚያስፈልገው ወይም በአጣዳፊ የስራ ስምሪት መከናወን ያለበት ስራ ሲያጋጥም፣ወይም በአንቀጽ-16 በተመለከተው መሰረት መብትና ግዴታው የተላለፈለት የከተማው አስተዳደር አካል ያልተጠናቀቀ ስራ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል በጊዜያዊነት በኮንትራት አመቺ የስራ ሁኔታ በመቅጠር ማሰራት ይችላል፤

ሰ) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በሥልጠና፣ በዓውደ ጥናትና በተዛማጅ ዘዴዎች ያከናውናል፤ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) ለከተማው አስተዳደር ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤

ቀ) ለሥራው እንቅስቃሴ ስኬታማነት ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ የአገር ውስጥና የውጪ አቻ ተቋማትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ሌሎች የመስኩ የምርምርና ስርፀት ተቋማት ጋር እንደአስፈላጊነቱ ግንኙነት ይመሰርታል፤

በ) በሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ፕላኖች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶች ጉዳዮች እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

ተ) አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችና በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ያለባቸው ሰዎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቸ)የፌደራል መንግስት ህግ በሚፈቅደው መሠረት በከተማው ውስጥ ተመዝግበው ለሚንቀሳቀሱ የከተማ ፕላን ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

2. May, notwithstanding the provisions of Sub-Article (f) (1) of this Article 7, deploy the necessary human resource based on temporary employment contract stipulating suitable working conditions in order to carry out activities that require particular professional ability or competence or have to be carried out urgently or to finalize unfinished functions of an organ of the city government whose rights and obligations have been transferred to the Commission as per Article 16;

g) carry out activities of capacity-building through trainings, workshops and other related methods, execute and cause the execution of activities of change and good governance and ensure their result-orienteers;

h) give assistance and advice to organs of the city government that implement and ensure the implementation of plans;

i) establish relations where necessary with equivalent domestic and external organs and higher education as well as study and research institutions that can lend assistance to the successful realization of its mandate;

j) ensure the inclusion of the affairs of women and the youth in the formulation of policies, laws, plans, programs and projects that it initiates;

k) facilitate conducive conditions within the purview of its mandate whereby persons with disabilities, elderly people, vulnerable sections of society and persons having HIV/AIDS in their blood can become users of equal opportunity and full participants;

ኀ) ፕላን በሚጥስ ማናቸውም ሰው ላይ በሕግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

ነ) የቦርዱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

ኘ) በፕላን፣ በሕግና በሌሎችም አግባብ ባላቸው የሙያ ዘርፎች የሚታወቁ ከፍተኛ ምሁራንና ባለሙያዎች እንዲሁም አግባብ ያላቸው የሲቪክ ማሕበራት ተወካዮችም ሆኑ የመሰረተ ልማት ግንባታ መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች የሚሳተፉበት የቴክኒክ ኮሚቴዎችንና ልዩ ልዩ መድረኮችን እንደያስፈላጊነቱ በማደራጀትና በማንቀሳቀስ ስራውን ያከናውናል፤

አ) ለሚሰጠው አገልግሎት በህግ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

ከ) ስለሥራው ክንውን ለከንቲባውና ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወቅታዊ ሪፖርት በህግ መሰረት ያቀርባል፤

ኸ) ውል ይዋዋላል፤የንብረት ባለቤት ይሆናል፤በስሙ ሊከሰስ ወይም ሊከስ ይችላል፤

ወ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የከተማው አስተዳደር አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪) ኮሚሽኑ ገፀምድራዊ ፕላንን በሚመለከት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ) ከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረታዊ የከተማ ካርታ ከሀገሪቱ ጂኦዴቲክ ካርታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ያደራጃል፤ያሰራጫል፤

ለ) የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ያዘጋጃል፣በከተማው ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

L) issue as per the stipulations of the relevant legislation of the federal government professional competence certificate for town planners who operate within the City;

m) take measure according to law on a person that violates plan;

n) serve as the Secretariat of the Board;

O) realize its functions by forming, and where necessary, operating technical committees and various forums in which high profile scholars and professionals renowned in the fields of plan, law and other relevant disciplines, as well as representatives of relevant civic organizations and governmental and nongovernmental organizations engaged in the construction of infrastructures participate;

P) collect charges according to law in respect of the service it renders;

Q) submit periodic reports of its work performance to the Mayor and to the Finance and Economic Development Bureau of the city government according to law;

R) Conclude contracts, own property, and may sue or may be sued in its name;

S) delegate to another organ of the city government a part of its power where necessary.

2) The Commission shall have the following specific powers and functions concerning spatial plan to:

a) prepare or ensure the preparation of the base map of the city in reference to the geodetic map of the country usable to prepare urban plan, and to organize and distribute same;

b) prepare the structural plan of the city and implement same when approved by the City Council;

ሐ) የአካባቢ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፣በከተማው ካቤኔ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ) የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሠ) የፀደቀ ፕላን በሕግ መሠረት እንደየአግባቡ ያሻሽላል፣ያጣጥማል፤

ረ) የከተማው የካባና ሌሎች ተቆፋሪ ማዕድናት ሥፍራዎች ያላቸውን የማዕድን ክምችት መጠን በከተማ ፕላን ላይ በግልፅ በሚያሳይ መልኩ እንዲመላከቱ ያደርጋል፤

ሰ) በፕላን ህግ በሚወሰነው መሰረት የከተማ ዲዛይን ዝግጅትና አፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፣ተፈፃሚ እንዲሆንም ያደርጋል፤

ሸ) የከተማው ነዋሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በከተማ ፕላን ዝግጅት፣ማሻሻል፣ማጣጣምና አፈጻጸም ሂደት በሕግ መሠረት በንቃት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቀ) የመዋቅራዊ ፕላን የተፈጻሚነት ዘመን ከማብቃቱ 3 ዓመት በፊት፣ ወይም የአካባቢ ልማት ፕላን ተፈፃሚነት ዘመን ከማብቃቱ 1 አመት በፊት፣ ተከታዩን ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል ፕሮጀክት በመቅረፅ ለከንቲባው ያቀርባል፤ሲጸድቅም ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ያደርጋል፤

በ) የፕላን፣የዲዛይንና የግንባታ ፈቃድ ደረጃዎችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፓርቶችን ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት እንዲያቀርቡና የመስክ ምልከታ እና ጥናት በማድረግ ሪፓርት ያቀርባል፤

ተ) የፀደቁ ፕላኖች የተፈለገውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል የአፈፃፀም ክትትልና የፋይዳ ግምገማ በየወቅቱ ያካሄዳል፤

ቸ) የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ባነሮችና ፅሑፎች የሚተከሉባቸውንና የሚለጠፉባቸውን ቦታዎች፣ግንባታዎችና ሌሎች ቋሚ ነገሮች ደረጃ አውጥቶ ይወስናል፡፡

c) prepare local development plan and to ensure the implementation thereof when approved by the City Cabinet;

d) prepare and approve integrated infrastructural plan and ensure the implementation thereof;

e) Undertake to amend plan according to law and submit it to be approved by the concerned organ, as well as decide on the adjustment of plan or submit the proposal of adjustment of plan to be approved as per the law;

f) mark out on urban plan the sites of queries and other extractable mines in such a manner that clearly shows their reserves;

g) issue urban design preparation and implementation guidelines and ensure the implementation thereof;

h) facilitate the active participation of the residents and other stakeholders of the city in the preparation , amendment and adjustment of an urban plan;

i) prepare and submit to the Mayor a project designed to prepare the forth-coming structural plan three years prior to the termination of the operative term of the existing one or a forth-coming local development plan one year prior to the termination of the operative term of the existing one, and implement the project when approved;

J) prepare and submit reports after having made sure that reports of plan implementing and regulatory organs are presented to it and having conducted site observations and studies; ;
(k) conduct periodic monitoring a evaluation in order to make sure that approved plans have brought about desired results;

L) study and determine the standards of sites, constructions and other structures where upon billboards, banners and other publicity scripts are erected and affixed;

፫) ኮሚሽኑ የሥነ ህዝብ፣ የማህበራዊና የምጣኔ ሀብታዊ እድገትና ልማት ፕላንን በሚመለከት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የተካሄዱ የስነህዝብ ትንበያዎችንና ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የከተማውን ዝርዝር የሥነ ህዝብ ጥናትና ትንበያ ያካሄዳል፣ውጤቱንም ለከተማው አስተዳደር አካላትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤የስነህዝብ ፖሊሲ በከተማው ውስጥ ይፈፅማል፣ያስፈፅማል፤

ለ) በአገር አቀፍ ደረጃ የተገመቱትን መነሻዎች መሰረት በማድረግ በፕላን የተቀመጠውን አመታዊ አጠቃላይ ከተማ አቀፍ የምርት እድገት ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት እድገት መነሻዎችን ይገምታል፣ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

ሐ) በአገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጡት ግቦች ማዕቀፍ ውስጥ ከሆኑ ከተማውን ከሚመለከቱ አጠቃላይ የምርት እድገት ግቦች የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንትና የወጪና የገቢ ንግድ ከተማ አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

መ) ከአጠቃላይ ከተማ አቀፍ ምርት የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎት ዘርፎችና የከተማ ግብርና የተናጠል ድርሻን ይለያል፣ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

3. The Commission shall have the following specific powers and functions in respect of demographic, social and economic development plans to:

a) conduct specific demographic studies and predictions of the city government based on nationwide demographic studies and predictions, and disseminate the results thereof to the organs of the city government and other stakeholders, as well as implement and ensure the implementation of the demographic policy within the city;

b) Conduct predictions of the indices of capital and productivity increase based on the indices of nationwide growth of products that is needed to generate annual overall citywide growth of products envisaged by plan and disseminate the results thereof to the organs of the city government and other stakeholders;

c) prepare citywide macro-economic objectives of saving, investment and growth of products of export and import which are within the framework of nationwide macro-economic objectives and compatible with citywide overall objectives of growth of products, policy and legal reform measures and follow up their implementation when approved;

d) identify the respective share of industry, service sector and urban agriculture out of the overall citywide products and disseminate the results thereof to the organs of the city government and other stakeholders;

ሠ) የፕላኑን ትግበራ ለመምራት እንዲያስችል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(መ) የተመለከቱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች ከንዑስ ዘርፎቻቸው እስከ ምርት ዓይነቶቻቸው ወይም የኢንዱስትሪ ክፍሎቻቸው ድረስ ይተነትናል፣ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

ረ) ከተማውን በተመለከተ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ግብዓቶችን አቅርቦት ለመተመን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፣ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

ሰ) ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

ሸ) ተዋረዳዊ አደረጃጀት ያላቸው የከተማው አስተዳደር ማዘጋጃ ቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ አካላት ቅርንጫፎች አንድን የዘርፍ አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በየበኩላቸው የሚፈፅሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን አፈፃፀም መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡

## ክፍል አራት
## የኮሚሽነሩና የምክትል ኮሚሽነሮች ተግባርና ኃላፊነት

### ፰. የኮሚሽነሩ ተግባርና ኃላፊነት

1) ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ ኮሚሽኑን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

e) analyze the economic sectors stipulated under Sub-Article (3) (d) of this Article from their sub-sectors down to the types of their products or industrial units and disseminate the results thereof to the organs of the city government and other stakeholders;

f) analyze the demand and supply of inputs that exists between the manufacturing industry and service sectors with a view to assessing the supply of domestic as well as external inputs concerning the city and disseminate the results thereof to the organs of the city government and other stakeholders;

g) prepare, through continuous consultations with the concerned organs of the city government, medium term and long term sectorial plans of social and economic development plan detailing feasible programs and projects as well as policy and legal reform measures that can be taken and follow up the implementation thereof when approved;

h) prepare integrated implementation program of medium term and long term social and economic development plans envisaging activities to be carried out by branches of municipal and non-municipal organs of the city government having downward strata of structures in order to to implement a sectorial plan in a manner that reinforces across the board and follow up the implementation thereof when approved.

## Part Four
## Functions and Responsibilities of the Commissioner and Vice Commissioner

### 8. Functions and responsibilities of the Commissioner

1) Being accountable to the Mayor, the commissioner shall manage and administer the Commission as the chief executive officer.



አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ 2445
Addis Negari Gazeta P.O.BOX 2445

፪) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ከቦርዱ ምክረ ሀሳብ ጋር ለከንቲባውና ለከተማው አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ወቅታዊ የስራ እንቅስቃሴ እና የሂሳብ ሪፖርት በህግ መሠረት ለከንቲባው እንዲሁም ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፤

መ) የኮሚሽኑን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የሰው ሀብት ፍላጎት፣ ደመወዝና አበል እንዲሁም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በማዘጋጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣በከተማው ካቢኔ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) ምክትል ኮሚሽሮችን በመምረጥ ለከንቲባው አቅርቦ ያስሾማል፣ "የስራ ዘርፍ ምደባቸውን ያካሂዳል፤ የሥራ ሃላፊዎችንና ሠራተኞችን ቅጥር፣ ምደባ፣ የደረጃ ዕድገትና ስንብት በሕግ መሠረት ይወስናል፤ውሳኔውም ተግባራዊ እንዲሆንም ያደርጋል፤

ረ) አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር ህግ መሰረት የኮሚሽኑን ንብረትና ገንዘብ ያስተዳድራል፣ እንደየአግባቡ ጥቅም ላይ ያውላል፤

ሰ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የኮሚሽኑን በጀት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ያንቀሳቅሳል፣ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

ሸ) የኮሚሽኑን ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የሚመሩትን የስራ ኃላፊዎች ይመድባል፣ ያነሳል፣ወይም ያሰናብታል፤

2. Without prejudice to the general statement of Sub-Article (1) of this Article, the commissioner shall have the following specific functions and responsibilities to:

a) Translate into action the powers and functions of the commission;
b) prepare and submit to the Mayor and to the Finance and Economic Development Bureau of the city government the annual activity and budgetary plans of the Commission together with the recommendations of the Board and to implement same when approved;
c) submit to the Mayor as well as to the Finance and Economic Development Bureau of the city government the periodic work performance and financial reports of the Commission as per the law;
d) prepare and submit to the Mayor the commission's organizational structure, human resource requirements, salaries and allowances as well as other benefits and implement same when approved by the City Cabinet;
e) select and propose vice commissioners for their appointment by the Mayor and assign each to the work division of the Commission, as well as decide on the employment, assignment, promotion and dismissal of those in charge and other employees according to law and ensure the execution thereof;
f) administer the property and money of the Commission and put it to use according to the relevant law of the city government and as appropriate ;
g) open bank accounts and operate the budget of the Commission as per the financial administration law of the city government and ensure the withdrawal of money and its utilization properly;
h) assign, remove or fire the heads to be placed to manage the branch offices of the commission;

ቀ) የኮሚሽኑን ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ማናቸውም የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ከሚገኝበት የአስተዳደር እርከን የአመራር አካላት ጋር በአስፈላጊው የሥራ መደጋገፍና ቅንጅት መስራቱንና በፕላን ዝግጅትና አተገባበር ረገድ ውሳኔ የሚሹ ቴክኒካዊና ሙያዊ ጉዳዮች በኮሚሽኑ በየደረጃው መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

በ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ኮሚሽኑን ይወክላል፣በኮሚሽኑ ስም ውል ይዋዋላል፤

ተ) የኮሚሽኑን ዓላማ ለማሳካት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በአጋርነት ይሰራል፣

ቸ) የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣የቦርዱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች የሚይዝና የሚያስፈርም ቃለ-ጉባኤ ፀሐፊ ይመድባል፤

ኀ) በዚህ አንቀጽ ከተሰጠው ስልጣን እና ሀላፊነቶች ላይ በከተማው ካቢኔ በሚጸድቀው የኮሚሽኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሰረት ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና መስጠት ይችላል፡፡

## ፱. የምክትል ኮሚሽነር ተግባር ሀላፊነት

እያንዳንዱ የዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1) የሚመደብበትን የኮሚሽኑ የሥራ ዘርፍ ይመራል፤

2) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ኮሚሽነሩ በሚሰጠው የጽሁፍ ውክልና መሰረት ተክቶት ይሰራል፡፡

h) oversee the work performance of branch offices of the Commission and ensure that a branch office of the Commission works in the necessary complementarily and integration with the decision-making bodies of the administrative stratum where it is situated and issues of plan preparation and implementation requiring professional and technical determination are dealt with at each level of the Commission;

i) represent the Commission in his relations with third parties and conclude contracts in the name of the Commission;

j) work in partnership with relevant bodies in order to achieve the purposes of the Commission;

k) work as a member and the secretary of the Board and assign a recording secretary who handles and facilitates the signature of the minutes of the board;:

l) Delegate to subordinate heads part of the functions and responsibilities entrusted to him by this Article based on the organizational structure to be approved by the City Cabinet.

## 9) Functions and responsibilities of vice Commissioner

Each vice commissioner shall be accountable to the commissioner and have the following functions and responsibilities:

**a)** manage the work division of the Commission to which he is assigned;

**b)** Replace and act on behalf of the commissioner in accordance with the written power of representation given by the commissioner where he is not available at work.

## ክፍል አምስት

## የቦርድ አመሰራረትና አሰራር

**፲. የቦርዱ አመሰራረትና ተዛማጅ ሁኔታዎች**

፩) ቦርዱ በሚከተለው መሰረት የሚመሰረት ይሆናል፡-

ሀ) ሰብሳቢውንና ፀሐፊን ጨምሮ ከሀያ እስከ ሀያ አምስት የሚሆኑ አባላት ይኖሩታል ፤

ለ) በከንቲባው ሰብሳቢነት የሚመራ ይሆናል፤

ሐ) ቃለ ጉባኤ ጸሐፊ ይኖረዋል፤

መ) ሌሎች አባላቱ በከንቲባው የሚሰየሙ ሆነው፣ ለከተማ ፕላንም ሆነ ለማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር ጠቃሚ ሙያዊና ቴክኒካዊ አስተዋፅኦ የማድረግ ብቃት ካላቸው ፣ከከተማው አስተዳደርና ከፌደራል መንግስት ለስራው መስከ አግባብነት ካላቸው አካላትና የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም በዘርፉ ከተሰማሩ ከፍተኛ ምሁራንና ባለሙያዎች የሚውጣጡ ይሆናሉ፤

ሠ) የከፍተኛ ምሑራንና ባለሙያዎች ጥንቅርና ተሳትፎ አመዛኝ ሊሆን በሚችልበት መልኩ የቦርዱ አባላት ዝርዝርና የሙያ ጥንቅራቸው በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ ለከንቲባው የሚቀርብ ይሆናል፡፡

፪) ከሰብሳቢውና ከፀሐፊው በስተቀር የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውም የቦርድ አባል ከአንድ ጊዜ በላይ በአባልነት ሊሰየም ይችላል፣የቦርድ አባል አገልግሎት ሲያበቃ ወይም ሲቋረጥ የአገልግሎት ምስክር ወረቀት በኮሚሽነሩ ይሰጠዋል፤

፫) የቦርድ ሰብሳቢ እና አባላት በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው መሰረት አበል ይከፈላቸዋል፡፡

## Part Five

## Formation and Operation of the Board

**10. Formation and related conditions of the Board**

1. The Board shall be formed as per the following:

a) It shall have 20 up to 25 members, including the chair person and the secretary;

b) It shall be presided by the Mayor;

c) It shall have a minutes recording secretary,;

d) The rest of its members shall be designated by the Mayor and drawn from among relevant city government and federal organs and civic societies that are engaged infrastructural development and competent to contribute professionally and technically in the preparation and implementation of spatial plans and socio-economic development plans, as well as high profile scholars and experts engaged in these fields;

e) Without prejudice to the majority of high profile scholars and experts, the shortlist of members and their professional composition shall be prepared by the commissioner and submitted to the Mayor.

2. The term of office of each Board member shall be three years, except for the chair person and the secretary; Where necessary, however, any Board member may be designated as member more than once; and each Board member shall be awarded by the commissioner certificate acknowledging his service at the end of his term or when his service stops before his term lapses;

3. The chair person and members of the Board shall be paid allowances as per the decision of the City Cabinet.

፲፩) የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት

፩) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ለኮሚሽኑ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ቦርዱ ፕላንን በሚመለከቱ ሞያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ኮሚሽኑን ያማክራል፣ሀሳቦችን ያመነጫል፣ይተቻል፤

፪)በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ቦርዱ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ቦርዱ በፕላን ዝግጅት፣ማሻሻል ወይም ማጣጣም ሂደት በኮሚሽኑ የሚቀርቡ ሰነዶችን በመመርመር ምክረ ሀሳቦችን ይሰጣል፣በሂደቱም የሚመለከታቸው የከተማ ነዋሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማድረግ፣ መደመጥና መብቶቻቸውም ሆኑ ሀሳቦቻቸው በህግ መሰረት ተገቢ ግምት ሊያገኙ ስለሚችሉበት ሁኔታ በሚሰጠው ምክረ ሀሳብ ተገቢ ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጋል፤

ለ) የኮሚሽኑን ወቅታዊ የስራ ክንውን ሪፖርቶችን መርምሮ ከፕላን ዝግጅት፣ማሻሻልና ማጣጣም እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ ጋር በተያያዙ ቁልፍ ችግሮች ላይ መክሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የሚያመላክቱ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ምክረ ሀሳቦችን ይሰጣል፤

ሐ) ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ህጋዊያን ተግባራትን በሚመለከት ምክረ ሀሳቦችን ይሰጣል፡፡

**11. Functions and responsibilities of the Board**

1) Without prejudice to the functions and responsibilities given to the commissioner by Article 8 of this Proclamation, the Board shall advice the commission in professional and technical matters concerning plans, initiate ideas and forward criticisms.

2) Without prejudice to the general statement of Sub-Article (1) of this Article, the Board shall have the following specific functions and responsibilities፡

a) provide recommendations after having examined documents submitted concerning the preparation, amendment or adjustment of plans, and ensure due regard to be given in its recommendations to conditions whereby the concerned residents of the city and other stakeholder organs can participate and be listened, and their rights and thoughts can be accorded due account;

b) to examine the periodic reports of the Commission, debate on key problems on the preparation, amendment and adjustment as well as monitoring and evaluation of plan implementation, and initiate ideas indicating directions of solutions of such problems and forward recommendations;

c) Forward recommendations concerning other juridical functions that help achieve the purposes for which the Commission is established.

፲፪) የቦርዱ ስብሰባ

፩) ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሳባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው በሚደረግ ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪) ከስብሰባው 3 ቀን በፊት የቦርዱ ስብሰባ ዓጀንዳ ለአባላት ከማድረስ ጋር የቦርዱ ስብሰባ ጥሪ ይተላለፋል፣አጀንዳ ማስያዝ የሚፈልግ አባል አጀንዳውን በስብሰባ ላይ ማስያዝ ይችላል፤

፫) በቦርዱ ስብሰባ ላይ ሃምሳ አንድ ከመቶ እና ከዚያ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤

፬) የቦርዱ ምክረ ሀሳብ በውሳኔ መልክ የሚተላለፈው በተባበረ ድምጽ፣ ይህ ሳይቻል ሲቀር ደግሞ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም፣ ድምጹ እኩል ከሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው የቦርዱ ምክረ ሀሳብ ይሆናል፤

፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም፣ከንቲባውም ሆነ ኮሚሽነሩ ምክረ ሀሳብ በተሰጠበት ጉዳይ በኃላፊነቱ መሰረት ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ የቦርዱን ምክረ ሀሳብ የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካለ፣ በምክረ ሀሳቡ አይገደድም፤

፮) የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ እንዲያዝና ጸደቆ በአባላት እንዲፈረም ይደረጋል፣የቃለ ጉባኤው ይዘት አስተዋጽኦ በጽሁፍ እየተዘጋጀ ለእያንዳንዱ ዓባል እንዲደርሰው ይደረጋል፤

፯) በዚህ አንቀጽ እና በሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቦርዱ ስለ አሰራሩ የራሱን ውስጠ ደንብ በማውጣት መስራት ይችላል፡፡

**12. Board meeting**

1) The Board shall meet once every three month; it shall, however, meet at any time upon the call of the chair person;
2) the meeting of the Board shall be called three days before it is held, provided that the call for the meeting is communicated to members together with the agenda thereof and a member who wants to propose agenda or item of agenda may also forward them;
3) The quorum of the meeting of the Board shall be formed with the attendance of 51 percent and more of its members;
4) The recommendations of the Board shall be passed by unanimous vote or, where not possible, by majority vote in the form of resolution; where the votes tie, the recommendation supported by the chair person shall consist in the recommendations of the Board;
5) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article, the Mayor or the commissioner shall not be obliged by the recommendations of the Board where he finds sufficient reason to reject the recommendations of the Board by the time he decides on a matter under his jurisdiction which the recommendations relate;
6) A summary of the agenda, recommendations and related matters of a meeting shall be prepared and handed to each member after the adoption and signing of the minutes of each meeting;
7) Without prejudice to the provisions of this Article and the law, the Board may issue rules of procedure and work accordingly.

፲፫) የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

፩.)ከንቲባው ቦርዱን በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፤ከ3ኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ቦርዱን ይወክላል፤

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ከቦርዱ ፀሐፊ ጋር በመመካከር የኮሚሽኑን የስብሰባ አጀንዳዎች ያዘጋጃል ወይም ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ ስብሰባ ከመደረጉ ቢያንስ 3 ቀን በፊት አጀንዳዎቹ ለቦርድ አባላት መድረሱን ያረጋግጣል፤

ለ) የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

ሐ) የቦርዱ ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ሲያስፈልግ፣ ጥሪው ለቦርድ አባላት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

መ) የቦርዱ ቃለጉባኤዎችና ሌሎች ሰነዶች በቦርዱ ፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) የቦርዱን ምክረ ሃሳቦች በአግባቡ በማጤን ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣ ወይም ውሳኔዎች እንደየአግባቡ መተላለፋቸውን ይከታተላል፡፡

**13. Functions and responsibilities of the Board Chairperson**

1) The Mayor shall preside over and coordinate the Board and represent it in relations with third parties.

2) Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Board chairperson shall have the following specific functions and responsibilities:

a) He shall prepare or cause the preparation and submission of meeting agenda in consultation with the secretary of the Board and ensure that the agenda together with the call for the meeting is communicated to board members three days before a meeting is held;

b) He shall chair the meeting of the Board;

c) He shall ensure that the meetings of the Board are held timely and a call for extraordinary meeting is made whenever such a meeting is found necessary;

d) He shall ensure that the minutes and other documents of the Board are organized and maintained properly by means of the Board secretary;

e) He shall pass decisions by duly taking the recommendations of the Board into account, or follow up whether decisions are passed as appropriate.

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፬) የበጀት ምንጭ**

የኮሚሽኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚውጣጣ ይሆናል፡-

፩) በከተማው አስተዳደር የሚመደብ በጀት፣ እና

፪) ከተለያዩ ሌሎች ህጋዊ ምንጮች የሚገኝ ገቢ፡፡

**፲፭) የሂሳብ መዝገብ**

፩) ኮሚሽኑ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ይይዛል፣ ያከናውናል፣ጠብቆ ያስቀምጣል፤

፪) የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በከተማው ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በሕግ መሠረት ይመረመራሉ፡፡

**፲፮) የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

የሚከተሉት የከተማው አስተዳደር ተቋማት መብትና ግዴታዎች ለኮሚሽኑ ተላልፈዋል፡-

፩) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 የተቋቋመው የከተማ ፕላን ኢንስቲቱት፤

## Part Six

## Miscellaneous Provisions

**14. Sources of Budget**

The Budget of the Commission shall be derived from the following sources:

1) Budget to be allocated by the city government; and

2) Revenues to be solicited from different sources of income.

**15. Records of accounts**

1) The Commission shall keep, maintain and store accurate and full records of accounts in accordance with the financial administration law of the city government;

2) The records of the accounts and monetary documents of the Commission shall be examined annually by the chief auditor of the city government or by external auditor to be designated by the chief auditor of the city government.

**16. Transfer of rights and obligations**

The rights and obligations of the following institutions of the city government are hereby transferred to the Commission:

1) the Plan Institute established by the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012;

፪) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 የተቋቋመው የከተማው አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከቱት የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባሮች ጋር በተያያዘ ተሰጥተውት የነበሩት ስልጣንና ተግባሮች እንዲሁም ከነዚህ ስልጣንና ተግባሮች ክንውን የተያያዘ የሰው ሀብትና ተዛማጅ ጉዳዮች፤

፫) በከተማው አስተዳደር ፕላን ክለሳ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 43/2004 የተቋቋመው የአዲስ አበባ ፕላን ክለሳ/መሪ ፕላን ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት እንዲሁም የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ የጋራ ልማት ፕላን ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት፡፡

**፲፯. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች**

፩) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 እንደተሻሻለ የሚከተሉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡-

ሀ) አንቀጽ 5(33) ፣አንቀጽ 29(12)፣ አንቀጽ 36(6)፣አንቀጽ 40 እና 42 ፤

ለ) አንቀጽ 29(14) ሥር "የረጅም፣የመካከለኛና" የሚሉት ቃላት፤

ሐ) አንቀጽ 35(2) ስር "የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩትን"የሚሉት ሐረግ፤

መ) አንቀጽ 66(17)(ሀ)(1)ስር "የአካባቢ ልማት ፕላን ያጠናል፣" የሚለው የድንጋጌው ክፍል፡፡

2) the powers and functions as well as human resource and related matters conferred on the Finance and Economic Development Bureau of the City Government established by the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012 in respect of the powers and functions entrusted to the Commission under Sub-Article (3) of Article 7 of this Proclamation;

3) The Master plan Project Office established by Addis Ababa Plan Revision Establishment Project Office Regulations No. 43/2011, and the Addis Ababa and Surrounding Oromia Special Zone Integrated Joint Development Plan Project Office.

**17. Repealed and Inapplicable laws**

1) The Following provisions of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012 (as amended) are hereby repealed:

a) Article 5(33), Article 29(12), Article 36(6), Articles 40 and 42(4);

b) the phrase, "long term, medium term and" under Article 29(12);

c) the phrase, "the Plan Institute of the city" under Article 35(2);

d) the clause, " study local development plan" under Article 66(17) (a) (1)

፪) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ክለሳ/መሪ ፕላን ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 43/2004

፫) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ አዋጅ፣ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ኮሚሽኑ በአግባቡ ተደራጅቶ በተሟላ ሁኔታ ስራ እስኪጀምር ድረስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተመለከቱት በስራ ላይ ያሉ አካላት ያልተጠናቀቁ ስራዎችን እያከናወኑ ይቀጥላሉ፤ በከተማው ከንቲባ በሚወጣ መመሪያ መሠረትም ለርክክብ ዝግጁ የሚሆኑበትና ኮሚሽኑ የሚረከብበት ስርአት እንዲኖርና ርክክብ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

**፲፱. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የከተማው ካቢኔ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

**፳. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በከተማው ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ 1 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም.

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

-

2) Addis Ababa Plan Revision/Master Plan Project Office Establishment Regulations No. 43/2011. ;

3) No Proclamation, regulations, directive or usage that is in conflict with the matters provided for by this Proclamation shall be effective.

**18. Transitional provisions**

operational organs indicated under Art. 16 of these proclamation shall resume carrying out activities that have not been completed until the Commission fully got started with its work after having been properly organized; and a system shall be put in place according to the directive to be issued by the Mayor of the city whereby such organs get prepared for hand over and it is made sure that the Commission takes over.

**19. Power to issue regulations**

The City Cabinet may issue regulations necessary to execute these regulations.

**20.Effective date of the proclamation**

This Proclamation shall be effective as of December 10, 2016.on which it is promulgated by the City Council.

Done at Addis Ababa this 10th day of December, 2016

Direba Kuma

Addis Ababa City Mayor